የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ጥር/2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ የተመደበለትን መደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለምአቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ መረጋገጫ( የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ወጪ፤**

1. ከግዥ መጠየቂያ ውጪ የሻተር ግዥ በብር 22,540.00 ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡
2. ደጋፊ ማስረጃ ያልቀረበለት የአበል ክፍያ ብር 34,429.00 ተገኝቷል፡፡
3. ከመመሪያ ውጭ በቀጥታ ለተፈፀመ የአገልግሎት ግዥ ብር 459,933.99 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
4. ግልፅ ጨረታ ሳይወጣ በውስን ጨረታ ለተፈፀመ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥ ብር 947,336.88 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
5. ለግንባታ ስራ ክፍያ በብልጫ ብር 25,543.13 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

6. በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 398,865.11

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30/2011ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች**

9. በኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት የሚወገዱ የተለያዩ አዳዲስ የተሽከርካሪ ጎማዎች ብዛት 75፤ አዳዲስ ፊለፖች ብዛት 86፤የኮምፒውተር (desk top) ብዛት 51፤ፕሮጀክተር ብዛት 5 እና ተመላሽ የመኪና ስፔርፓርቶች፤ ሞተር ሳይክሎች ብዛት 2፤የተለያዩ የእጅ መታጠቢያ ሲንኮች ብዛት 6 ሲሆኑ በአጠቃላይ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተከማችተው መገኘታቸው።
10. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ምዝገባ፤ አያያዝ፤ ስምሪት እና አጠቃቀምን የሚያሳይ ቅጽ 02 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑበኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

ከሠላምታ ጋር

ትዕግስት ረታ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር